# <u>የኮፈሌው ካሕን ጥሪ</u>

ከሊ.ማ. አበባው ይግዛው

በአርሲ ክፍለ ሀገር፣ በኮፈሌ ወረዳ ተፈጸመ የተባለውን አሳዛኝና አሳፋሪ ድርጊት የሰማሁት በኀዘን ነው። ያንንም አሳዛኝ ድርጊት መነሻ በማድረግ አንዳንድ መሰረታዊ የእስልምና መመሪያዎችን ለማንሳት እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በዘመነ ብሉይ ኪዳንን፣ በዘመነ ሐዲስ ሐዲስ ኪዳንን፣ በዘመነ ቁርዓንም እስልምናን ተቀብላ ኦሪታዊያንን ክርስቲኖችንና ሙስሊሞችን አቅፋ የኖረች ቅድስት ሀገር መሆኗ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ታሪክ የተመሰከረ ነው። ቤተ አይሁድ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ መስጊድ በኢትዮጵያ የተከበሩ የአምልኮ ቦታዎች ናቸው። የሁሉም መልእክት ሰዎች እግዚአብሔርን የማመን፣ ስሙን እንዲቀድሱ፣ ክብሩን እንዲወርሱ፣ በመካከላቸውም በወንድማማችነትና በእህትማማችነት ተከባብረውና ተፈቃቅረው እንዲኖሩ ነው። የብሉይ ኪዳን ዐሠርቱ ቃላት፣ የሐዲስ ኪዳን ስድስቱ ቃላት፣ በቁርአን አምስቱ ቃላትና ክልክል፣ ሐራም የሆኑ ሃያው ትዕዛዛት እነዚህን ለመፈጸምና ለማስፈጸም በግልጽ የተመዘገቡና ለአማኖች የታዘዙ ተወራራሽ የዕምነት መመሪዎች ናቸው። ታዲያ እነዚህን ተላልፎ ሰውን መግደል፣ ንብረቱን ማቃጠል፣ በተለይም እግዚአብሔር የሚገለገልበትን ቤተ መቅደስ በእሳት መለኮስና የሌላውን እምነት ማንኳስ በሁሉም ሃይማኖቶች ከባድ ኃጢአት ሲሆን በዓለማዊ ሕግም ታላቅ ወንጀል ነው። ይህንን በሃይማኖት ስም የሚፈጽሙ ካሉ ወይም ሃይማኖታቸውን አያውቁም ያለዚያም ጭፍን የፖለቲካ መሳሪያዎች ሆነዋል ማለት ነው። ነቢዩ ሙሐመድም «ሐበሾችን አትንኩአቸው!» አሉ እንጅ ከነቤተ ክርስቲያናቸው አቃጥሉአቸው አላሉም። በታሪክ እንደሚታወቀውና በቁርአኑ መቅድም ተጽፎ እንደሚገኘው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እስላሞች ችግር ሲጸናባቸው ያጽናኑ፣ ፍርድ የበየኑ እንጅ ጠላቶች አይደሉም። ይህንንም ለማስረዳት ታላቁ መምህር ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ በሚል ርእስ በጻፉት መጻፉቸው ቁሬሾች በመጀመሪያዎቹ የሙስሊሙ እምነት ተከታዮች ላይ ስቃይ ሲያጸኑባቸው ነቢዩ ሙሐመድ የሰጡትን መመሪያ ከገጽ 45 እስከ 47 ዘግበውት ይገኛል። አቶ በላይ አባይም «የኢትዮጵያ ሥልጣኔ» በሚለው መጽሐፋቸው ከገጽ 145 እስከ 146 የሚከተለውን ጽፈዋል፦

...ከዚህ ቀደም ብሎ ነቢዩ ሙሐመድ ወገኖቹና የቅርብ ተከታዩቹ ሃይማኖቱን ባልተቀበሉ ሰዎች ስለተሰቃዩበት «ራሳችንን ለመከላከል አላህ ብርታቱን እስኪሰጠን ድረስ ወደ ሐበሻ አገር (ኢትዮጵያ) ሄዳችሁ እዚያው ቆዩ። የሐቀኞችና የጻድቃን ሀገር ናት። ንጉሷም ፍርድና ፍትሕ ዐዋቂና አስተዋይ ስለሆነ በሱ ዘንድ ማንም አይበደልምና አትስጉ» በማለት ምክር ሰጣቸው። እነኝህ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የነቢዩ ሙሐመድን ምክር ለበስ ትእዛዝ በመቀበል ዐሥራ ሁለት ወንዶችና አራት ሴቶች የሚገኙበት የመጀመሪያው ቡድን በ610 ዓ.ም. ቀይ ባህርን አቋርጦ መጠጊያ ለማግኘት ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ከመጡትም ስደተኞች መካከል የሙሐመድ ሴት ልጅ ሩቂያና ባለቤቷ የሙሐመድ ሶስተኛ የሆኑት ከሊፋ ዑስማን ይገኙባቸዋል። ኢትዮጵያዊው ንጉሥ አርማህ (አስባሐ) (603 - 623 ዓ. ም.) ስደተኞችን ከተቀበላቸው በኋላ የሚኖሩበት ቦታ ሰጥቶ በጥገኝነት እንዲቆዩ ፈቀደላቸው። ስደተኞቹም ከሶስት ወር ቆይታ በኋላ ነገሩ ሁሉ ተረጋግቶ አገር ሰላም ሆኗል በሚል የሐሰት ወሬ ተገፋፍተው ወደ መካ ተመለሱ። ነገር ግን ጭቆናው ከቀድሞ የባሰ ስለሆነ ወዲያውኑ ሌሎቹ ሰማንያ ሶስት ወንዶችና ዐሥራ ስምንት ሴቶች እንዲሁም ሕፃናት ጨምረው ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። የአክሱም ንጉሥም መስተንግዶ አድርጎ ከተቀበላቸው በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀመጡ ፈቀደላቸው።

«ስደተኞቹ ኢትዮጵያ ከደረሱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ጥገኞቹን መልሰው በእጅ ለማስገባት በማሰብ የመካ ቁሬሾች በርካታ ስጦታዎችን የያዙ ባለሥልጣን የሆኑትን መልእክተኞች ወደ ንጉሥ አርማህ ላኩ። ንጉሡ ግን የክርስቲያን ዻዻስና መሳፍንት ባሉበት የቁሬሾችን መልእክተኞና እስላሞቹን አቅርቦ ጉዳያቸውን ጠየቃቸው። የሁለቱን ወገን ሐሳብ ከሰማና ከመረመረ በኋላ «ተራራ የሚያህል ወርቅ ብትሰጡኝም እንኳ በኔ ሀገር የመጡትን ሰዎች መልሼ አልሰጣችሁም» በማለት መልእክተኞቹ ያመጡትን ስጦታ ይዘውት እንዲመለሱ አዘዛቸው። ስደተኞቹንም «በግዛቴ ያለሥጋት መኖር ትችላላችሁ» አላቸው። ይህም የኢትዮጵያውያንን እንግዳ ተቀባይነትን ባህልንና ለተቸገሩ መጠለያ የመስጠትን ልማድ የሚያንጸባርቅ ጠባይ ነው። ስደተኞቹም ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላምና በምቾት እምነታቸውን እንደያዙ ለዐሥራ አምስት ዓመታት ቆዩ። ይኸውም በዓለም አቀፍ የስደተኛ መብት መጠበቅ የተጀመረው በዚያን ጊዜ በአክሱም መንግሥት እንደሆነ በታሪክ ጸሐፊዎች ሰርክ ሲነገር የኖረ ሐቅ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የመንፈስ ኩራት ሊሰማን ይገባል። ኢትዮጵያ የጎረቤት ሀገሮች ሕዝቦች መብት ጠባቂ ለመሆንዋም የታሪክ ማስረጃ ነው።»

እንግዲህ በኢትዮጵያ በክርስቲያኖች እና በእስላሞች መካከል የተፈጠረው ሃይማኖታዊ ግንኙነት ይህን ሲመስል ለዘመናት በሰላም ኖረዋል። እስላሞችና ክርስቲያኖች አብረው የማይኖሩበት አካባቢ በኢትዮጵያ መሬት የለም። እንኳን የከፋ ችግር ሳይኖር ቢኖርም እንኳ ተቻችሎ፣ ተፈቃቅሮ መኖርን የሁሉም ሃይማኖት ያዛል። የአዳም ዘር እንዲፋቀር ያስተምራል።

ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ በመጽሐፋቸው አማኞች ሊጠነቀቁባቸው ግዴታ ከሆኑ ብዙ ነገሮች ውስጥ ክልክል የሆኑ ነገሮች (ሐራም ነገሮች) አንስተው በቁ.2 «አማኝን (በፈጣሪ ያመነን) አውቆ የገደለ ቅጣቱ ዘለዓለም ገሐነም ነው»፣ በቁ13 ደግሞ «መስደብ ክልክል ነው። በግልጥ መስደብም ሆነ ባሸሙር መቆንጠጥ፣ ባይን ጥቅሻ፣ በከንፈር ንክሻ ማሾፍ፣ መዝለፍ በጥብቅ የተከለከለ መጥፎ ነገር ነው። እነዚህ ነገሮች ብዙ ጉዳት የሚያስከትሉ የሰላም ጠንቅ፣ የማህበራዊ ኑሮ ተውሳክ ናቸውና መጠንቀቅ ይገባል። አንዳንድ ጊዜ እመማታትና እመገዳደል ያደርሳሉ» ብለዋል። በተጨማሪም፦

በቁጥር 19ም «ሰውን መበደል (ዙልመኛነት) ክልክል ነው። በሰው ላይ ግፍ መስራት፣ መብቱን መንካት፣ ን
ብረቱን ማበላሸት፣ ያለአግባብ ገንዘቡን መብላት፣ ወይም ማስበላት፣ ክብሩን ማዋረድ ትልቅ በደል ነው። ሊ
ሰራ የማይገባው ነውና መጠንቀቅ ያስፈልጋል» ሲሉ ጽፈዋል። ሊሰሩ የሚያስፈልጉና ማንኛውም እስላም ሊፈ
ጽማቸው ግዴታ የሆኑ ነገሮችንም ሲያስገነዝቡ፦

በቁ. 4 «ለጎረቤት ታማኝና ቅን መሆን፣ ዕቃን ማጋደድ፣ በችግሩ ሁሉ መርዳት አስፈላጊ ነው። በሌለበት ጊ
ዜ ንብረቱን በታማኝነት መጠበቅ በጥብቅ የታዘዘ ነው። <u>የጎረቤቱን እምነት </u> የማይጠብቅ ሙአሚን (ያመነ)
አይደለም» ሲሉ ነቢዩ ሙሐመድ የተናገሩትን ጠቅሰዋል።

ቀ.5. «ለማንኛውም ሰው ወይም እንሰሳት ማዘንና መራራት፣ ለተቸገረ ሁሉ መርዳት አስፈላጊ ነው። በሐዲስ
(በነቢዩ ሙሐመድ) ቃል እንዲህ ይላል፦ «ለርኅሩኆች አላህ ይራራቸዋል። በምድር ሳላችሁ እራሩ፣ በሰማይ
ያለ ይራራላችሁ ዘንድ» የተባለውንም አስገንዝበዋል።

ቀ.7. «እርስ በርስ መተባበርና መፈቃቀር በማህበራዊ ኑሮ መተጋገዝና ላንድነት መተሳሰር አስፈላጊ ነው። በሌ
ላ ሰው ላይ የሚደርሰውን ችግርና መከራ ልክ ባንተ ላይ እንደደረሰብህ አድርገህ ማየትና መቆርቆር፣ ሌላው
ሰው የሚያስደስት ነገር ሲያገኝ አንተ እንዳገኘኸው ያህል መደሰት አለብህ» የሚለውን አብራርተዋል።

ቁ. 8. «በእድሜ የሚበልጥህን፣ የበላይህን ማንኛውንም ሰው ማክበር ፣ ከበታችህ ላሉት ማዘንና መራራት በጣ
ም አስፈላጊ ነው። ነቢዩ ሙሐመድ «ታላቁን የማያከብር ለታናሹ የማይራራ ወገናችን አይደለም» ብለዋል።

ቁ. 10. <u>ቁጭትን መዋጥ (መታገስ)</u> - ለበደለህ ሰው ይቅርታ ማድረግ በቁርአን ስለታዘዘ አስፈላጊ መሆኑንም ገ
ልጸዋል።

ቀ.20. «ከስህተት መመለስ (መቶበት)፣ ንሥሐ መግባት አለብህ። ከኃጢአት በወደቅህ ጊዜ ቶሎ ብለህ መመ
ለስና መጸጸት፣ አጠፋሁ ማረኝ ብለህ ፈጠሪህን መለመን አለብህ። አጥፍተህ እንዳላጠፋህ መሆን አይገባህም
የሚሉትንና ሌሎችንም የቁርአን ትእዛዛት በሰፊው ጽፈዋል።

ታዲያ አሁን በኮፈሌ የተፈጸመውን አረመኔያዊ ድርጊት የፈጸሙት የምን እምነት ተከታዮች ናቸው? እውን
እስላሞች ናቸው? እኔ እጠራጠራለሁ።

ነቢዩ «የጎረቤቱን እምነት የማይጠብቅ ሙአሚን (ያመነ) አይደለም» ሲሉ ተናግረዋልና። ይህን ያነበበና በቁር
አን አምናለሁ የሚል እስላም ከላይ የተጠቀሱትን ትእዛዛት አልፎ ሽማግሎችን ካረደ፣ ቤተክርስቲያንን አቃጥ
ሎ ምዕመናንን ካሳደደ ሙአሚን አይደለም። ንሥሐም አልገባ፣ ኃጢአቱ አይሠርየለትም፣ ወንጀሉም አይፋ
ቅለትም።

ነቢዩ ሙሐመድ ውለታቸውን ቆጥረው በጀሐድ እንኳ ሐበሾችን አትንኳቸው ያሉትን ትእዛዝ ሽሮ የአረመኔነት
ስራ መስራት በአምላክ አይደለም፣ ዳኛ ቢገኝ በምድር ህግም ያስቀጣል። አነስ ባለው ክርስቲያን ላይ በዛ ያ
ለው እስላም ይህን አይነት አሳፋሪ ስራ የሚሰራ ከሆነ ከዚያም ላይ ቤት እሳት አለ» እንደሚባለው ይህ በጥቂ
ት ጥጋበኞች የተጫረው እሳት በህግ ካልተገታ አገር ሊያቀጣጥል ይችላል። የማንም መሳሪያ በመሆን ሃይማ
ኖትን ሽፋን አድርጎ መወንበድ ለአገራችን አይበጅም። የሚበጀን እንደ አባቶቻችን ታቻችለን፣ ተፈቃቅረን
መኖር ብቻ ነው። መንግስትም ሆነ የሃይማኖት አባቶች ሳይዘገይ ይህን አሳፋሪ ድርጊት ማረም አለባቸው።
ነቢዩ እንዳሉት ትልቁም ሥርየት ንስሐና እርቅ ስለሆነ የሃይማኖት አባቶች ግራ-ቀኙን ማስታረቅና ለንስሐ ማብ
ቃት አለባቸው። A. J. Grant የሚባል የእንግሊዝ ታሪክ ጸሀፊ «ግጭቶች ሁሉ ክፉዎች ናቸው። የሃይማኖት
ግጭቶች ግን ከሁሉም የከፉ ናቸው።» "All wars are cruel, but religious wars are the cruellest of
all." በማለት የጠቀሰውን ማስታወስ ይገባናል።

«ቁጭ ብለው የሰቀሉት ቁሞ ለማውረድ ያስቸግራል» ይባላልና በአካባቢው የሚገኙ የፖለቲካ ሰዎች ሃላፊነታ
ቸውን በሚገባ ሊወጡ ይገባል። ቤተክርስቲያናቸው የተቃጠለባቸውና ከሞት የተረፉት ካህን በጀርመን ሬዲዮ
ያሰሙት ቃል ይሰቀጥጣል። «ምፅአት የመጣ መሰለኝ። ህዝብ በህዝብ ላይ ይነሳል የሚለውና ሌሎች በቅ
ዱሳት መጻህፍት የተመለከቱት የአለም ፍጻሜ ምልክቶች የደረሱ መሰለኝ። እባካችሁ በውስጥም በውጭም
ያላችሁ ጽልዩልን። ሌላ መፍትሄ ያለው አይመስለንም» በማለት ስለደረሰው አሳፋሪ ድርጊት ሲያብራሩ በጣ
ም ያሳዝናል። በቤተክርስቲያንም ሆነ በመንግስት መሪዎች ተስፋቸው ተሟጧል።

በውነትም ጸሎት የሚያስፈልገበት ጊዜ ነው። ከመርዶ በቀር የሚሰማ የምስራች ወሬ የለም። በውነቱ ጉዳዩን
በጥሞና ሲያጤኑት ግራ ያጋባል። የአርባ ጉጉው ጭፍጨፋ ተቀጥላ ይመስላል። እነዚህ ክርስቲያኖች ዘራቸ
ው እንዳይጠፋ ጸሎት ብቻ ሳይሆን ፍጡን ረድኤት ያስፈልጋቸዋል። የተፈናቀሉት ቢቻል እንዲታረቁ፣ ባይ
ቻል በአሉበት እንዲቋቋሙ የህግ ከለላ ያስፈልጋቸዋል። ጉዳዩ በቀላሉ የሚታይ አይመስለኝም።

የተፈራ ዋልዋ አፍ እንዳመጣ ኋላ ቀር ቅስቀሳ ማቀጣጠል በሌላም ቦታ የባሰ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ዜጎ
ችን በሃይማኖት መለያየት በተለይ ማርክሲዝም ሌኒንዝምን አነበብን ከሚሉ የተሐድሶ ልጆች የሚጠበቅ አይደ
ለም። በተለይ የአካባቢው መሪዎች ግብራቸው እንደስማቸው ወደ ዱላነት ካዘነበለ ከማይወጡት ጣጣ ውስጥ
መከረኛውን ህዝብ ይዘው ይገባሉ፤ መጨረሻቸው ላያምር።